# Global Storybooks

globalstorybooks.net

## ውሳኔ


Ursula Nafula
Vusi Malindi
Mezemir Girma



This work is licensed under a Creative Commons Attribution 4.0 International License.

https://creativecommons.org/licenses/by/4.0


# ውሳኔ


Ursula Nafula
Vusi Malindi
Mezemir Girma


2

አማርኛ am

መንደሬ ብዙ ችግር ነበረባት። ውሃ ከቦኖ ለመቅዳት ረጅም ሰልፍ እንሰለፍ ነበር።

በሌሎች ሰዎች የሚሰጠንን ምግብ እንጠብቅ ነበር።

ሌባ ፍራቻ ቤቶቻችንን በጊዜ እንዘጋ ነበር።



ሁላችንም በአንድ ድምጽ ‹‹ህይወታችንን መቀየር ይኖርብናል›› በማለት ጮህን። ከዚያች ቀን ጀምረን ችግሮቻችንን ለመፍታት አብረን እንሰራ ጀመር።

ሌላ ሰውዬ ተነሳና ‹‹እኛ ወንዶቹ ጉድጓድ መቆፈር እንችላለን›› አለ።



ብዙ ልጆች ትምህርታቸውን ያቋርጡ ነበር።

ወጣት ሴቶች በሌሎች መንደሮች ውስጥ በሰራተኝነት ያገለግሉ ነበር።



አንዲት ሴትዮም ‹‹ሴቶቹ ከኔ ጋር እህል መዝራት ላይ መሰማራት ይችላሉ›› አሉ።

ግንድ ላይ የተቀመጠው የስምንት ዓመቱ ዓመቱ ጁማ ‹‹እኔ በማጽዳት እረዳለሁ›› ሲል ተናገረ፡፡



ግማሾቹ ወንዶች ልጆች በየሰፈሩ እየዞሩ ሲውሉ፤ ሌሎቹ ደግሞ በሰው ማሳ ላይ ያገለግሉ ነበር፡፡

ነፋስ በነፈሰ ቁጥር ቆሻሻ ወረቀት በየአጥሩና በየዛፉ ላይ ይንጠለጠል ነበር።



አባቴ ተነስቶ ‹‹እነዚህን ችግሮቻችንን ለመፍታት በጋራ መስራት ይኖርብናል›› አለ።

ሰዎች ከአንድ ትልቅ ዛፍ ስር ተቀምጠው ያዳምጡ ጀመር።



ሰዎችን በጥንቃቄ ጉድለት የተጣለ ብርጭቆ ይቆርጣቸው ነበር።

አንድ ቀን ውሃው ቆመና የውሃ መያዣዎቻችን ባዶ ቀሩ።



አባቴ ሰዎች በመንደር ስብሰባ ላይ እንዲገኙ ለመቀስቀስ ከቤት ቤት ዞረ።